ሾልኮ የወጣው የብልፅግና ድብቅ ሰነድ



የብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ

(ለብልፅግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የቀረበ)

የካቲት 2014 ዓ.ም

ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

መግቢያ

እኛ የብልጽግና ፓርቲ አባላት የአገራችን ኢትዮጵያን እድገትና የጋራ ብልጽግና እውን ለማድረግ በመነሳት፣ አገራችንን ወደሚቀጥለው ምዕራፍ ለማሻገር አዲስ ራዕይና አዲስ ትርክት እንደሚያስፈልግ በማመን፣ የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፤ የግለሰብና የቡድን መብቶች በሚዛኑ የሚከበሩባት፤ ዜጎች ከድህነት ተላቀው በብልጽግና የሚኖሩባት፤ ጠንካራና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚታይባት፤ በአህጉራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊው መድረክ ላይ ጉልህ ሚና የምትጫወት ኢትዮጵያን ለማየት ባለን ተስፋ፣

የበለጸገች፣ ሕብረ-ብሔራዊ ማንነቷ የዳበረና አንድነቷ የተጠናከረ ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ባለን ቁርጠኝነት፣

ይህንንም ለመተግበር በመደመር አስተሳሰብና በአንድነት ቅኝት በመነሳት፣ ልናያት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የእያንዳንዳችንን ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳትና የበኩላችንን ሚና ለመጫወት በከፍተኛ ቆራጥነት ተሰባስበን መታገል በማስፈለጉ፣

የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) የሚመራበት የመተዳደሪያ ደንብ መቅረጽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተደነገጉትን ሕጎች የሚያከብር የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) ሰነድን በመጀመሪያ ጉባዔያችን መክረንበት ሕጋዊ የፓርቲውን ሰነድ አድርገን አጽድቀናል።

ምዕራፍ አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ “የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) መተዳደሪያ ደንብ” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2. የፓርቲው መጠሪያ

የፓርቲው መጠሪያ “የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)” ነው።

አንቀጽ 3. የፓርቲው ዓርማ

1. የአርማው ቀለምና አቀማመጥ

በክብ ነጭ መደብ ውስጥ በስተግርጌ ጥቁር ቀለም ያላቸው ለማቀፍ የተዘጋጁ ሁለት የሰው እጅ ምስሎች ያሉት ሲሆን፣ መሀል ላይ ለማቀፍ የተዘጋጁ የሰው እጅ ምስሉ ውስጥ ሆነው የሚታዩ ሦስት የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ሦስት ሰዎች የሚገኙበት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈነጥቁ ቢጫ ቀለም ያላቸው የብርሃን ፍንጣቂዎችን በውስጡ አካቶ ያያዘ ነው።

2. ጥቅል ትርጉም

ዓርማው የአገራችንን ሕብረ-ብሄራዊነትን፣ አገራዊ አንድነትን፣ ብሄራዊ ኩራት፣ ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና የብልፅግናን አስተሳሰብ የያዘ ሆኖ ከውስጥ ወደ ውጭ እየሰፋ የሚሄድ የቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ትስስሮችን የሚያመላክት ነው።

3. ዝርዝር ትርጉም

1. እጅ፡- በሎጎው በስተግርጌ በኩል የተቀመጠው የሰው የእጅ ምስል ብልፅግና ሁሉን አቃፊ መሆኑን የሚወክል ሲሆን ቀለሙ ጥቁር የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያዊያን የጥቁር ህዝቦች የነፃነትና የድል ተምሳሌት መሆናችንን የሚወክል ነው።

2. የሰዎች ምስል፡- ብልፅግና ሰው ተኮር ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ሲሆን ፓርቲው ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ብልፅግና የሚታገል መሆኑን ይወክላል። የሰዎቹ ምስል ቀለማቸው የተለያየ መሆኑ የኢትዮጵያን ብዝሃነት እንዲያሳይና ብዝሃነታችን የውበታችንና የጠንካራ አንድነታችን ምልክት ሆኖ ተወክሏል።

3. ጎህ፡- ከላይ የተቀመጡት የብርሃን ፍንጣቂዎች ጎህን የሚወክሉ ሲሆን ጎህ ጨለማን ሰንጥቆ የሚመጣ ብርሃን እንደመሆኑ መጠን ብልፅግና ኢትዮጵያን ወደ ከፍታና የብርሃን

ዘመን ለማሸጋገር የሚታገል ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ነው። (የተስፋና የብልፅግና ዘመንን ይወክላል)።

አንቀፅ 4. የፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች

1) ፓርቲው ለሁሉም የሀገራችን ቋንቋዎች ሙሉ ዕውቅና ይሰጣል፤

2) በፌደራል ደረጃ የፓርቲው የሥራ ቋንቋ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት እና ክልሎች በሕገ-መንግስታቸው የሥራ ቋንቋ አድርገው ያፀደቋቸው ቋንቋዎች ይሆናሉ።

3) የፓርቲው የየደረጃው ጽ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ

ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የሥራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም ይችላሉ።

አንቀጽ 5. የፓርቲው ልሳን

1) የፓርቲው ልሳን ስያሜ “ብልፅግና” ነው።

2) የፓርቲው ልሳን በፓርቲው የሥራ ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ብዝኃን ልሳን ነው።

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የሀገሪቱና የውጭ ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል።

አንቀጽ 6. የፓርቲው ጽሕፈት ቤት

1) የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ፊንፊኔ ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፓርቲው በክልል፣ በከተማ አስተዳደር፣ በዞን፤ በወረዳና በቀበሌ ጽሕፈት ቤቶች ይኖሩታል፤

3) እንደአስፈላጊነት በውጭ ሀገር ጽሕፈት ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል።

አንቀጽ 7. የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሖች፣ ዕሴቶችና የአሠራር ሥርዓት

1) የፓርቲው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) ጠንካራ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ቅቡልነት ያለው፣ ዘላቂ ሀገረ መንግሥት መገንባት፤

ለ) ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት፤

ሐ) ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያሰፍን ማኅበራዊ ልማትን ማረጋገጥ

መ) ሀገራዊ ክብርንና ጥቅምን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት ማካሄድ

2) የፓርቲው መርሖች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) ሕዝባዊነት፤

ለ) ዴሞክራሲያዊነት፤

ሐ) የሕግ የበላይነት፤

መ) ልማትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት፤

ሠ) ተግባራዊ እውነታ፤

ረ) ሀገራዊ አንድነትና ህብረ ብሔራዊነት፤

3) የፓርቲው ዕሴቶች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) የዜጎችና የሕዝቦች ክብር፣

ለ) ፍትሕ፤

ሐ) ወንድማማችነትና እህትማማችነት፣

ሠ) መከባበርና መቻቻል፤

ረ) ጎበረ ብሔራዊ አንድነት፤

4) የፓርቲው የአሠራር መርሆች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) ፓርቲው የሀገሪቱንና የክልሎችን ሕገ-መንግሥትንና ሌሎች ሕጎችን በማክበር ተግባራቱን ያከናውናል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የፓርቲው አባላት የመፈጸም፣ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፤

ሐ) አባላት የግል ሐሳባቸውን የማራመድ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፓርቲውን ውሳኔ የመፈጸምና የማስፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፤

መ) ማንኛውም አባል በፓርቲ ውስጥ እኩል ድምፅና በውሳኔ ሂደቶች ውስጥ አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፤

ሠ) የፓርቲ ውሳኔ በየደረጃው ዴሞክራሲያዊ ውይይት ከተካሄደበትና የጋራ ግንዛቤ ከተያዘበት በኋላ በተባበረ ድምፅ እንዲወሰን ጥረት ይደረጋል።

ረ) በተባበረ ድምፅ ለመጽደቅ ባልቻሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፤ ተፈጻሚነቱም በወሰነው አካልና በታችኛው መዋቅር ላይ ይሆናል፤

ሰ) በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የፓርቲው ውሳኔ የሚያልፈው በአብላጫ ድምፅ ነው። የተሰጠው ድምፅ ለሁለት እኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምፅ አሸናፊ ይሆናል።

ሸ) በዚህ ደንብ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የየትኛውም የፓርቲው መዋቅር ምልዐተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጠቅላላው የጉባኤው ወይም የስብሰባው ተሳታፊዎች ውስጥ 50% +1 እና ከዚያ በላይ ሲገኙ ነው፤

ቀ) በሁሉም ስብሰባዎች በተለይም አስቸኳይ ስብሰባዎች ሁሉም የሚመለከታቸው አባላት የመገኘት ግዴታ አለባቸው። ሆነ ብሎ ምልዓተ-ጉባኤ እንዳይሟላ ማድረግ የተከለከለ ነው፤ ምልዓተ-ጉባኤ እንዳይሟላ ያደረገ በዲሲፕሊን ጥፋት ይጠየቃል፤

በ) በየትኛውም ደረጃ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ከተሰብሳቢ አባላት መካከል 1/3ኛ የሚሆኑት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ካቀረቡ፣ ጥያቄው ለውይይት ክፍት ሆኖ እንደገና ውሳኔ ይሰጥበታል፤

ተ) በአንድ መድረክ ላይ በተወሰነ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ቀርቦ፣ ውሳኔው በድጋሚ በዚያው መድረክ ተቀባይነት ካገኘ፣ ድጋሚ አቤቱታ አይቀርብም። በጉዳዩ ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው በተግባር እየፈጸሙ በሂደት በሚከፈት የጉባዔ/ ኮንፈረንስ አጋጣሚ ወይም የጽሑፍ ፊርማ በማሰባሰብ ብቻ ይሆናል።

ቸ) እንደገና ይታይልን የሚል ጥያቄ ሲቀርብ፣ የወሰነው አካል በጉባዔ ላይ ከሆነ፣ በቃል ወይም በጽሑፍ አቤቱታው ቀርቦ፣ ጉዳዩ ከላይ በተቀመጠው መሠረት ይታያል። ወሳኙ አካል ጉባዔውን/ስብሰባውን ፈፅሞ ከተበተነ በኋላ ግን አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በጽሑፍ ብቻ ይሆናል።

ኀ) አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ለሰብሳቢው ያቀርባል። ሰብሳቢው አቤቱታውን ወደሚመለከታቸው አባላት ሁሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሠራጨት አቤቱታውን የሚደግፉ ሁሉ እንዲፈርሙ ያደርጋል። ከሚመለከታቸው አባላት ውስጥ 1/3ኛው ከፈረሙ፣ ጉዳዩ በሚቀጥለው መደበኛ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ላይ እንዲታይ ይደረጋል።

ነ) ሁሉም የፓርቲው አሠራሮች በግልጽነትና ዴሞክራሲያዊነት ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ፣

ኘ) በፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካላት የሚወሰኑና በሀገሪቱና በሕዝቦቿ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳርፉ አቋሞችና ውሳኔዎች ሁሉ ውሳኔውን ባስተላለፈው አካል በምስጢር ተጠብቆ እንዲቆይ ካልተወሰነ በስተቀር ከአስፈላጊው ማብራሪያ ጋር ለአባላትና እንዳስፈላጊነቱ ለሕዝብ ይገለጻሉ።

አ) በፓርቲዉ ጉባዔዎች፣ ኮንፈረንሶችና ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በቃለ- ጉባዔ ተይዘዉ፣ ፀድቀዉ ይቀመጣሉ።

ከ) በልዩ ሁኔታ በምስጢርነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉ የፓርቲ ጉዳዮች የሚለዩበት አሠራር ይዘረጋል።

ኸ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አመራር አካላት ለወሰኗቸው ውሳኔዎች በተናጠልና በጋራ በሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ። በተጨማሪም ኃላፊነትን ያለመወጣት ወይም ከተሰጠ ኃላፊነት ውጪ መሠማራት ተጠያቂነትን ያስከትላል።

ወ) ተጠያቂነትም እንደሁኔታው በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም በሀገሪቱ ሕጎች መሠረት ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ርምጃዎችን ያስወስዳል።

ዐ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አካላት የሥራ እንቅስቃሴያቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ዕቅድና ሪፖርት በወቅቱ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፤ የበላይ አካላትም ወቅታዊ ግብረ መልስ መስጠት አለባቸው።

ዘ) አባላትና አደረጃጀቶች የሥራ አፈጻጸም ውጤታማነታቸውን የሚመዝኑባቸውና እርስ በርስ የሚማማሩባቸው መደበኛ የውይይት ጊዜያት ይኖራቸዋል።

ዠ) ፓርቲው አባላቱ፣ አመራሩና መዋቅሩ ላሳዩት የላቀ አፈጻጸም ዕውቅናና ሽልማት የሚሰጥበት የአሠራር ሥርዓት ይከተላል፤

የ) ፓርቲው በሁሉም ደረጃዎች የወጣቶችና የሴቶች አደረጃጀቶችን የማሳተፍና የማብቃት አቅጣጫና አሠራርን ይከተላል።

ደ) ፓርቲው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ላሉት በማዕከላዊነት የሚወሰን ሆኖ፤ እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያ በታች ባሉት የፓርቲው አደረጃጀት ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል።

ጀ) ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የጎብረተሰብ ክፍሎች የፓርቲው አባላትና አደረጃጀቶች በየደረጃው ተገቢውን ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

ገ) የፓርቲው ዓላማዎች፣ ፕሮግራምና ዕቅድ ተግባራዊ የሚሆኑት በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት፣ በክልል፣ በከተማ አስተዳደርና በየደረጃው ባሉ የፓርቲ ጽ/ቤቶች፣ የፓርቲ አደረጃጀቶችና በውጪ ሀገር በሚኖሩ የፓርቲው መዋቅሮች አማካኝነት ይሆናል።

ጠ) በፓርቲው አባላትና እጩ አባላት በሚፈጸሙ ጥፋቶች ላይ የሚወሰደው የዲስፒሊን ርምጃ የፓርቲውን ሥነ ምግባር ለማዳበር፣ ስሕተቶችንና ጉድለቶችን ለማረምና የፓርቲውን ጥራትና ጥንካሬ ለመጠበቅ የሚያገለግል ሊሆን ይገባል።

አንቀጽ 8. የፓርቲው የምርጫ መርህና የአሠራር ሥርዓት

1) የፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች እንዲሁም የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ ምርጫ ግልፅ፣ ነጻና ፍትሐዊ እንዲሁም በምስጢር በሚሰጥ ድምፅ የሚመረጡ ይሆናሉ፣

2) በፓርቲው ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚደረጉ ምርጫዎች የጾታ ተዋፅዖን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል፤

3) ማንኛውም የፓርቲ አባል በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (8)(ሠ) በወጣው የፓርቲ የምርጫ የአሠራር ሥርዓት መሠረት በሀገሪቱ በሚካሄዱ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሚያና የድጋሚ ምርጫዎች ፓርቲውን ወክሎ የመወዳደር መብት አለው።

ምዕራፍ ሁለት

አባልነት

አንቀጽ 9. የፓርቲው አባል ስለመሆን

1) ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በጽናት ተግባራዊ ለማድረግ ፍቃደኛ የሆነ፣

ለ) መልካም ሥነ ምግባር ያለውና በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያለው፣

ሐ) በኅብረ ብሔራዊነትና በሀገራዊ አንድነት ላይ ፅኑ አቋም ያለውና ዋልታ ረገጥ አመለካከትና ተግባሮችን በጽናት የሚታገል፣

መ) ዜጎችንና ሕዝቦችን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የሕዝብ ጥቅምን የሚያስቀድም፣ከሙስናና ብልሹ አሠራሮች ራሱን ያራቀና ሌሎችንም የሚታገል፣

ሠ) የፓርቲውን ዕሴቶችና ዓላማዎችን ተቀብሎ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኛ የሆነ፤

ረ) ወርኃዊ የገንዘብ መዋጮ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ፤

ሰ) እድሜው አሥራ ስምንት ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣

ሸ) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፣

ቀ) የፖለቲካ ድርጅት አባል የመሆን መብቱ በሕግ ያልተገደበ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተገፈፈ፤

በ) በዚህ ደንብ በተወሰነው መሠረት የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።

2) የአባልነት የእድሜ ጣሪያንና የክብር አባልነትን የተመለከተ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴው ይወጣል።

አንቀጽ 10. ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ

1) አንድ የፓርቲው አባል ለመሆን የወሰነ ዜጋ በአካባቢው ለሚገኘው የፓርቲው ጽሕፈት ቤት በጽሑፍ ማመልከት ይኖርበታል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው መዋቅርና አባል ለፓርቲው ፕሮግራምና መተደደሪያ ደንብ ታማኝና ለተግባራዊነቱም ይታገላል ብሎ ያመነበትን ግለሰብ ለፓርቲው አባልነት ሊመለምለው ይችላል፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት መሥፈርቱን አሟልቶ የተመለመለ ግለሰብ ለስድስት ወራት በሙከራ አባልነት ይቆያል፤

4) የፓርቲው መሠረታዊ ድርጅት ወይም ሕዋስ የእጩ አባሉን አፈጻጸም አይቶ ሙሉ አባል የማድረግ ወይም ተጨማሪ ከሶስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ የእጩነት ጊዜውን ማራዘም ይችላል፣

5) የእጩ አባልነት ቆይታ ከአንድ ጊዜ በላይ አይራዘምም፣ ከክትትል ሂደትም ይሠረዛል፤

6) እጩ አባሉ በሙከራ ጊዜ ቆይታው ፓርቲው የሚሰጠውን ተልዕኮ ይፈጽማል፣

7) የአባላት ምልመላ፣ ግንባታ፣ ሥምሪት፣ ምደባ፣ ምዘናና ስንብት ዝርዝር መመሪያ በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ይወጣል።

አንቀጽ 11. የአባል መብት

1) ማንኛውም የፓርቲ ሙሉ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፣

ሀ) በፓርቲው አካላት ምርጫዎች የመምረጥና የመመረጥ፣

ለ) በፓርቲው ጉባኤዎች የመሳተፍ፣ በውይይት የመካፈልና በድምፅ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ድምፅ የመስጠት፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በሕጋዊ መድረኮች ሐሳቡን በፅሑፍም ሆነ በቃል የማቅረብ፣

ሐ) በማንኛውም የፓርቲ አካል ወይም አባል ላይ በተቻለ መጠን በመረጃ የተደገፈ ገንቢ ሂስ የማቅረብ፣

መ) በየትኛውም የፓርቲ ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በየደረጃው ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፤

ሠ) ስለራሱ፣ ስለአካሉ፣ ስለፓርቲው ማወቅ የሚገባውን ነገር እስከ ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ የመጠየቅና መልስ የማግኘት፣

ረ) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ፕሮግራም፣ አቋሞችና ውሳኔዎች ለሌሎች የማሳወቅ፣ የማስተዋወቅ፣ የማስረፅና በተጨባጭ እንዲተገበር የማድረግና

ሰ) በየትኛውም ጊዜ በጽሑፍ አመልክቶና በእጅቹ የሚገኙ የፓርቲው ንብረቶችን ኃላፊነት በተሞላበት አግባብ አስረክቦ መልቀቅ ይችላል።

2) ማንኛውም እጩ አባል በየደረጃው ለፓርቲው አካላት የመምረጥና የመመረጥ እንዲሁም ድምፅ የመስጠት መብት የለውም፤ የሌሎች የአባልነት መብቶች ግን ተጠቃሚ ነው፣ የግዴታዎችም ተገዥ ይሆናል።

አንቀጽ 12. የአባል ግዴታ

1. ማንኛውም የፓርቲ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

1) በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ በፓርቲ ሕግ መሠረት የፀደቁትን የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶችን የማወቅ፣ የመቀበል፣ የማክበር፣ የመገዛትና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል፣

2) በሚገኝበት የሥራ መስክና የኃላፊነት ደረጃ የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ፣ የፓርቲውን የፖለቲካ ዕሳቤዎች ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ፣

3) የፓርቲውን መርሖች፣ ዕሴቶችና የአባላት የሥነ ምግባር ሕጎችን ማክበርና የፓርቲውን፣ የሕዝብና የሀገርን ደኅንነትና ሉዓላዊነት የመጠበቅ፣

4) የሀገሪቱን ሕጎችና ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ውሳኔዎችን ማክበር፣

5) የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የሚጎዱ ማናቸውንም ዝንባሌዎችና ድርጊቶችን የማጋለጥና የመታገል፣

6) በፓርቲው ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች የተያዙ ተናጠል ዐቋሞችን የፓርቲው በማስመሰል በማናቸውም መልኩ በሚዲያ ከማሠራጨት የመቆጠብ፣

7) በአባላት መካከል የሚኖረውን መልካም ግንኙነት ከሚያጎድፉ ድርጊቶች የመታቀብ፣

😎በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 8(ተ) እንደተገለጠው ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው የአባልነት መዋጮ ዓይነትና አከፋፈል መመሪያ መሠረት የአባልነት መዋጮ የመክፈል፣

9) የፓርቲውን ንብረት በአግባቡ የመጠበቅ፣

10) ከሙስና የጸዳ፣ ሙስናንና አድሏዊ አሠራርን የመታገልና የማጋለጥ ግዴታና

11) ከአንድ አካባቢ ወይም የሥራ ቦታ ወደሌላ አካባቢ ወይም የሥራ ቦታ በቋሚነት ለቅቆ ሲሄድ የለቀቀበትን እና የደረሰበትን የፓርቲ መዋቅር ማሳወቅ፣ የፓርቲውን ንብረት እና ሰነዶችን ለለቀቀበት አካባቢ የፓርቲ መዋቅር ማስረከብ አለበት።

አንቀጽ 13. በአባላት ላይ በዲስፒሊን ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

1) ማንኛውም አባል በሚከተሉት ሁኔታዎች ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ከአባልነት እስከ ማሰናበት የሚደርስ ርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፤

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ያላከበረ ወይም ሌሎች ጥፋቶችን የፈጸመ አባል ወይም እጩ አባል ጉዳዩ በዝርዝር ታይቶ እንደጥፋቱ ክብደት የዲስፒሊን ርምጃ ይወሰድበታል፣

ለ) ማንኛውም አባል የፓርቲውን የአባልነት መዋጮ በተከታታይ ለ6 ወራት አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ካልከፈለና ውዝፍ መዋጮውን ለመክፈል ፍቃደኛ ካልሆነ ከአባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ይቆጠራል፣

ሐ) ማንኛውም አባል በትክክለኛ መረጃ ላይ ሳይመሠረት አባላትን ከመለመለ ወይም ከአባልነት ካገለለ፣ አባላትንም ከወነጀለ በዲሲፕሊን ጥፋት ይጠየቃል፣

መ) ማንኛውም አመራር ወይም አባል የሐሰት ሪፖርት መስጠትም ሆነ መጠቀም ክልክል ነው፣

ሠ) በፓርቲው ውስጥ አንጃነት እና ቡድነተኝነት መፍጠር ወይም ማስፋፋት ክልክል ነው፣

ረ) ማንኛውም አባል የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆኑ ከተደረሰበት ከፓርቲ አባልነቱ ይሰረዛል፣

ሰ) የፓርቲው አባላትና እጩ አባላት የሚፈጽሟቸው ጥፋቶች ክብደት እየታየ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፤

1. ለሙሉ አባል፡-

ሀ) ተግሳጽ፣

ለ) የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

ሐ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

መ) ከኃላፊነት ማገድ፣

ሠ) ከኃላፊነት ማነሣት፣

ረ) ከአባልነት ማገድ፣

ሰ) ከአባልነት መሠረዝ፤

2. ለእጩ አባል

ሀ) የእጩ አባልነት ለአንድ የሙከራ ጊዜ ማራዘም፣

ለ) ከእጩ አባልነት መሠረዝ፤

ሸ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ርምጃ የተወሰደበት አባል ወይም እጩ አባል አቤቱታውን በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር አቅርቦ በውሳኔው ካልረካ በየደረጃው ላለው የፓርቲ የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል፣

2) የአባላት የዲስፒሊን ጉድለት ርምጃ አወሳሰድ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፤

ምዕራፍ ሦስት

የፓርቲው አወቃቀርና አደረጃጀት

አንቀጽ 14. የፓርቲ አወቃቀርና የአመራር አካላት

1) የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የሀገሪቱን ሕገ-መንግሥታዊ ፌዴራላዊ አወቃቀር የተከተለ ነው፤ በዚሁ መሠረት የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) ፌዴራል፣

ለ) ክልል፣

ሐ) ዞን/ከተማ/ክፍ ከተማ/ልዩ ወረዳ/ቀበሌ

2) ፓርቲው የሚከተሉት ተቋማዊ መዋቅሮች ይኖሩታል፡፡

ሀ) ጉባዔ፣

ለ) ማዕከላዊ ኮሚቴ፣

ሐ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣

መ) ፕሬዚዳንት፣

ሠ) ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት፣

ረ) ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣

ረ) የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን፣

ሰ) የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት

ሸ) የፓርቲው የክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች፣

ቀ) የፓርቲው የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ ጽሕፈት ቤቶች፣

3) የፓርቲው መሠረታዊ ድርጅቶችና ሕዋሳት አባላት በሚገኙባቸው ቦታዎች ይቋቋማሉ፡፡

አንቀጽ 15. የፓርቲው ጉባኤ፣ የክልል፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ የኮንፈረንሶች አወቃቀር

1) የፓርቲው ጉባዔ በፌዴራል ደረጃ ይቋቋማል፤

2) በክልል ደረጃ ክልላዊ ኮንፈረንስ የሚኖር ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ከዞን እስከ ቀበሌ ኮንፈረንሶች ሊዋቀሩ ይችላሉ፤

3) የኮንፈረንስ ውክልና በዋናነት የአባላትን ብዛት መሠረት ያደረገ ሆኖ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ቁጥር ያላቸውን የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አባላት ውክልና ባረጋገጠ መልኩ ይዋቀራል፤

4) በመደበኛ ጉባዔና በእያንዳንዱ ኮንፈረንስ ወቅት ከሚመረጡ ጉባዔያተኞችና የኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ብቃት ያላቸውን አዳዲስ አባላት ያካተተ ይሆናል።

አንቀጽ 16. የፓርቲው ጉባዔ

1) የፓርቲው ጉባዔ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው፤

2) የፓርቲው ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ዓመት ተኩል አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣ የጉባዔው የመካሄጃ ጊዜ ከሦስት ዓመት መብለጥ የለበትም፤

3) ጉባዔው በፕሬዚዳንቱና በተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ስብሳቢነት ይመራል፤

4) የጉባዔው ተሳታፊዎች ቁጥር ከ500 በላይ ሆኖ ስብጥሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸውን የጎበረተሰብ ክፍሎች ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ ይፈጸማል፤

5) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ቢያንስ በ1/3ኛው በድምፅ ብልጫ ሲወስን በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

6) የፓርቲው የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን የቋሚ ጉባዔ አባላትን 1/3ኛ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ሊያደርግ ይችላል።

7) የፓርቲው ጉባዔ አስቸኳይ ስብሰባ ሲጠራ ቀድሞ በተካሄደው መደበኛ ጉባዔ የተካፈሉት ጉባዔያተኞች በቀጥታ ይሳተፋሉ።

😎ለመደበኛ የፓርቲው ጉባዔ ከአባላቱ መካከል ቢያንስ 2/3ኛው በስብሰባው ላይ ሲገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

9) የአስቸኳይ ጉባዔ ስብሰባ ምልዓተ-ጉባዔ 50 % +1 ነው።

10) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት በቀጥታ በጉባኤው ስብሰባ ይሳተፋሉ፤

11) የፓርቲው ጉባዔ አባላት ውክልናና ተሳትፎ የሕዝብና የአባላትን ቁጥር መሠረት ያደረገ ሆኖ ዝርዝሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፤

12) ለመደበኛ ጉባዔና ለአስቸኳይ ጉባዔ የጉባዔዎቹ ጊዜ፣ ቦታና አጀንዳዎችን አስቀድሞ በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በኩል መገለጽ አለበት፤

አንቀጽ 17. የፓርቲው ጉባዔ ተግባርና ኃላፊነት

1) የፓርቲው ጉባዔው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ይቀይራል፤

ለ) ፓርቲው የሚመራባቸውን አጠቃላይ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ያስቀምጣል፤

ሐ) የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ቁጥር ይወስናል፤

መ) የማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የኢንስፔክሽንና የሥነ-ብግባር ኮሚሽንና እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች አካላት የሚቀርቡለትን ሪፖርቶች ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ያጸድቃል፤

ሠ) ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር የሚያደርገውን የውሕደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሐሳብ ያፅድቃል፤

ረ) የማዕከላዊ ኮሚቴና የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ዕገዳና ስንብት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ሰ) የፓርቲውን ሥምና ዓርማ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይለውጣል።

ሸ) ጉባዔው መደበኛው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በዝግጅት ኮሚቴ የሚቀርብለትን የጉባዔ ዝግጅት ሪፖርትና የስብሰባውን የሥነ ሥርዓት ደንብ መርምሮ ያፀድቃል፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባዔው ከተግባርና ኃላፊነቱ በሙሉ ወይም በክፊል ለማዕከላዊ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

አንቀጽ 18. የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ

1) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባዔ ሆኖ ከጉባዔ እስከ ጉባዔ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ አካል ነው።

2) ማዕከላዊ ኮሚቴው በቀጥታ በነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከጉባዔው አባላት በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ በሚመረጡ አባላት የሚመሠረት ነው፤

3) የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ብዛትና ስብጥር በሕዝብ ብዛትና በአባላት ቁጥር መሠረት ሆኖ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴ ይወጣል፤

4) ማዕከላዊ ኮሚቴው በየስድስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ካመነበት ወይም ከማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት መካከል አንድ ሦስተኛ ሲጠይቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

5) የማዕከላዊ ኮሚቴ ምልዐተ-ጉባኤ ከአባላቱ ከ 50% +1 የተገኙበት ይሆናል፤

6) በማዕከላዊ ኮሚቴ የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ ከፓርቲው ቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን ውጪ በሁሉም የፓርቲው መዋቅሮችና አካላት ተፈጻሚ ይሆናል፤

7) የማዕከላዊ ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዚዳንት እና/ወይም ፕሬዚዳንቱ በወከለው ምክትል ፕሬዚዳንት በጋራ ይመራል፤

😎ማዕከላዊ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ፣ የጉባዔው ውሳኔዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

ለ) በፓርቲው ጉባዔ በሚቀመጠው አቅጣጫና ውሳኔዎች መሠረት ፓርቲውን በበላይነት ይመራል፤ የፓርቲውን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አቅጣጫዎችና ዕቅዶችን እንዲሁም የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን ያመነጫል፣ አፈጻጸማቸውን በየጊዜው ይገመግማል፤

ሐ) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ በሚሹ ነጥቦች ላይ ይወስናል፤

መ) በፓርቲው ፕሬዚዳንት የተፈፀመን የስምምነት የውሳኔ ሐሳብ ያፀድቃል፤

ሠ) የፓርቲውን የምርጫ የአሠራር ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፤

ረ) የምርጫ ስትራቴጂ ያጸድቃል፣ ለምርጫ የሚደረገውን ሂደት የሚመራ የምርጫ ኮሚቴ ያቋቁማል፤

ሰ) አስፈላጊ የሆኑ ድርጅታዊ መዋቅሮችን ይዘረጋል፤

ሸ) የሥራ አስፈጻሚና የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን ቁጥርና ስብጥር ይወስናል፤

ቀ) ከአባላቱ መካከል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የፓርቲውን ፕሬዝዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንትና ፕሬዝዳንቶችን ይመርጣል፤

በ) የማዕከላዊ ኮሚቴውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና የፓርቲውን በጀት ያፀድቃል፤

ተ) የፓርቲ አባላት የመዋጮ ዓይነት፣ መጠንና አከፋፈል በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤

ቸ) በፓርቲው መተዳዳሪያ ደንብ ትርጓሜ ላይ ለሚነሡ ክርክሮች ውሳኔ ይሰጣል፤

ነ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ሁሉ ያከናውናል፤

ኘ) የፓርቲ ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴ ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ከኢንስፔክሽንና ከሥነ-ምግባር ኮሚሽን በተውጣጡ አባላት ያዋቅራል፤ (ተሰረዟል፣ ለምን)

አ) ለፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ ተገዢ ያልሆኑና የአመራር ብቃት የጎደላቸውን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን በ2/3ኛ ድምፅ ያግዳል፤

ከ) ደንቡን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ያጸድቃል፣

9) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (😎 (ሀ-ከ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማዕከላዊ ኮሚቴው ከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

አንቀጽ 19. የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

1) የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ፤ በማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል በምስጢር ድምፅ ይመረጣል፤

2) የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዚዳንት ይመራል።

3) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤

4) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዚዳንቱ ወይም ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት 1/3ኛው ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል፤

5) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምልዓተ-ጉባኤ ከአባላቱ ከ50%+1 የተገኙበት ይሆናል፤

6) የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

ሀ) በጉባዔውና በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚወጡ ዕቅዶች፣ አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች መከበራቸውንና በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ አመራር ይሰጣል፣

ለ) የጉባዔውንና የማዕከላዊ ኮሚቴውን አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ የጎብረተሰቡ ኑሮ እንዲሻሻልና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር እንዲቻል አስፈላጊውን ስልት ይቀይሳል፣ መመሪያ ይሰጣል፣ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

ሐ) ሕብረ ብሔራዊ አንድነታችንን የሚያጠናክሩና የፌዴራል ሥርዓቱን የሚያጎለብቱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፤ መተግበራቸውን ይከታተላል፤

መ) የጉባዔውና የማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔዎች ሕገ ደንቡን መሠረት በማድረግ የፓርቲውን የውስጠ ድርጅት ዴሞክራሲ የበለጠ ለማዳበር የሚያስችሉ መመሪያዎችን ከቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን ጋር በመመካከር ያወጣል፣ ተግባራዊ መሆናቸውንም ይከታተላል፣

ሠ) ለማዕከላዊ ኮሚቴው የሥራ ዕቅድና ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አመራር የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

ሰ) ለፓርቲው ጽ/ቤት የዕለት ተዕለት የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤

ሸ) በፓርቲው የአመራር መዋቅር የአመራር ምደባ ያካሄዳል፣ የአፈጻጸም መመሪያ በማውጣት ይፈጽማል፣

ቀ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

በ) የፓርቲው ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ለፓርቲው አባላትና ለመላው ሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ከ(ሀ-በ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለፓርቲው ፕሬዚዳንት ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

አንቀጽ 20. የፓርቲው ፕሬዚዳንት

1) የፓርቲው ፕሬዚዳንት ተጠሪነቱ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

ሀ) የማዕከላዊ ኮሚቴና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፤

ለ) የማዕከላዊ ኮሚቴና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ሐ) የማዕከላዊ ኮሚቴና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ያስፈጽማል፤

መ) ፓርቲውን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣ ስምምነቶችን ይፈርማል፤

ሠ) የሥራ ሪፖርቱን ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ያቀርባል፤

ረ) ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጉባኤዎች አጀንዳ ያዘጋጃል፤

ሰ) በማዕከላዊ ኮሚቴውና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

አንቀጽ 21. የፓርቲው ምክትል ፕሬዚዳንቶች

1) ፓርቲው እንድ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንትና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይኖሩታል፤ የምክትል ፕሬዝዳንቶች ብዛት በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚወሰን ይሆናል።

2) ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል:-

ሀ) ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ በፕሬዚዳንቱ የተወከለው ምክትል ፕሬዚዳንት ተክቶ ይሠራል፣

ለ) በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በፕሬዚዳንቱ በሚሰጧቸው የሥራ ስምሪት መሠረት ሥራቸውን ያከናውናሉ።

አንቀጽ 22. የፓርቲው የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን

1) የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ከፓርቲው ጉባዔ በሚመረጡ አባላት ይዋቀራል፤ የኮሚሽኑ አባላት ብዛት በጉባዔው የሚወሰን ሆኖ የሕዝብ ብዛትና የአባላትን ቁጥር እንዲሁም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የጎበረተሰብ ክፍሎችን ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ ርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችል አግባብ እንዲዋቀር ይደረጋል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል ፤

2) ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባኤ ነው፤

3) የኮሚሽኑ አባላት ከሥራቸው ጋር የሚጋጭ የፓርቲ ምደባ አይሰጣቸውም፤

4) ኮሚሽኑ ቋሚ ጽሕፈት ቤትና ባለሞያ ሠራተኞች ይኖሩታል፤

5) ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አደረጃጀት ጽሕፈት ቤቶች ያደራጃል፤ የራሱን መዋቅር ይዘረጋል፤

6) ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ኮሚሽኑ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

ለ) የጉባዔ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በአግባቡ መፈጸማቸውን ይከታተላል፣

ሐ) የፓርቲው አባላትና እጩ አባላት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ ማክበራቸውን፣ ለጠበቀ ዲስፕሊን ተገዢ መሆናቸውን ይከታተላል

መ) የፓርቲው ሥራዎች ከፓርቲው መሠረታዊ መርሖችና መተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም ሌሎች መመሪያዎች አኳያ መፈጸማቸውን ይከታተላል፤

ሠ) የፓርቲውን ጥራትና ጥንካሬ ለማዳበር አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣

ረ) የፓርቲው አባላትና አካላት መብቶችና ጥቅሞች መከበራቸውን ይከታተላል፤

ሰ) ከአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል፣ የእርምት የውሳኔ ሐሳቡን ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሸ) የፓርቲው ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መጠበቃቸውን ቁጥጥር ያደረጋል፤ የፓርቲው አባላት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፤

ቀ) ለፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ ተገዢ ያልሆኑ የኮሚሽን አባላትን በ2/3ኛ ድምጽ ያግዳል፤

ተ) ይህን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በማድረግ የኮሚሽኑን የአሠራር መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፤

ቸ) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱን ለጉባኤው ያቀርባል፤

7) ኮሚሽኑ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል።

😎ኮሚሽኑ የራሱን ዓመታዊ ዕቅዶች እያዘጋጀ ተግባራቱን ይመራል።

9) በኮሚሽኑ የሚቀርበውን የእርምት ሐሳብ የሥራ አስፈጻሚው ካልተቀበለው ለማዕከላዊ ኮሚቴው ይቀርባል፤ ማዕከላዊ ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እስከ ጉባኤ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል።

10) ኮሚሽኑ ከመካከሉ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ጸሐፊውን መርጦ ለጉባኤው ያሳውቃል።

አንቀጽ 23. የፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት

1) ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ የፓርቲውን የፖለቲካ፣ የድርጅት፣ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመራል፣ የጥናትና ምርምር ማዕከል ሆኖ ያገለግላል።

2) ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና ምክትል ኃላፊዎች ይኖሩታል፤

3) ጽሕፈት ቤቱ በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርት አዘጋጅቶ ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል፤

4) እጩ የክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችን፣ ከየክልሉ የፓርቲ አመራሮች ጋር በመሆን ከለየ በኋላ ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ለውሳኔ ያቀርባል፤

5) የዋና ጽሕፈት ቤትንና የየደረጃ የክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶችን ዝርዝር አሠራርን አስመልክቶ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ረቂቅ መመሪያ ያቀርባል፤

6) ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዕቅዶችን፣ ውሳኔዎችንና ሌሎች በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ የፓርቲውን ሥራዎች ያቅዳል፣ ያስፈጽማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ለ) የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

ሐ) የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የሕዝብ ግንኙነት፣ የጥናትና ምርምርና ሌሎች ተግባሮችን ይፈጽማል፤

መ) በፕሬዚዳንቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ፓርቲውን ወክሎ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፤

ሠ) ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር የፓርቲውን ልሣን ዋና አዘጋጅና የቦርድ አባላትን ይሰይማል፣

ረ) የጸደቀውን የፓርቲ በጀት ያስተዳድራል፤

ሰ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈጻጸም እና ዕቅዶችን በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሣሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃል፤

ሸ) በፓርቲው ስም ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

ቀ) በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

በ) የፓርቲ ጉባዔ ቦታ፣ ጊዜና አጀንዳ አዘጋጅቶ ሲወሰን ለሚመለከተው ፓርቲ አደረጃጀት ያሳውቃል፤

ተ) በፓርቲው አማካሪ ጉባዔ ሥራዎችን ያስተባብራል፣

ቸ) በማዕከላዊ ኮሚቴ፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ ደንብ መመሪያ እንዲዘጋጅላቸው የተመለከቱና ሌሎች ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መመሪያዎችን በፓርቲው አማካሪ ጉባኤ አማካኝነት በማስጠናት ለፕሬዚዳንቱ ያቀርባል።

😎የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤቱ ከተግባርና ኃላፊነቱ ለክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

ምዕራፍ አራት

የፓርቲው የክልል አደረጃጀት

አንቀጽ 24. የፓርቲ አደረጃጀትና አወቃቀር

1) ለፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ የክልል የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች የክልል ስያሜ በመያዝ እንደሚከተለው ተቋቁመዋል።

ሀ) የብልጽግና ፓርቲ የኦሮምያ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ለ) የብልጽግና ፓርቲ የአማራ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ሐ) የብልጽግና ፓርቲ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጽሕፈት ቤት፣

መ) የብልጽግና ፓርቲ የሶማሌ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ሠ) የብልጽግና ፓርቲ የትግራይ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ረ) የብልጽግና ፓርቲ የአፋር ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ሰ) የብልጽግና ፓርቲ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ሸ) የብልጽግና ፓርቲ የጋምቤላ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ቀ) የብልጽግና ፓርቲ የሐረሪ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

በ). የብልጽግና ፓረቲ የሲዳማ ክልል ጽሕፈት ቤት፣

ቸ). የብልጽግና ፓርቲ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ጽሕፈት ቤት ናቸው።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የድሬዳዋ አስተዳደር የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ይቋቋማሉ፣ እንዲሁም በየደረጃው የክፍለ ከተማና የወረዳ/ቀበሌ አደረጃጀቶች ይኖራቸዋል።

3) ለክልል የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ተጠሪ የሆኑ የዞኖች፣ የወረዳዎች/ልዩ ወረዳዎች፣ የከተሞች እና የቀበሌዎች ጽሕፈት ቤቶች ይኖሩታል፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) የተቋቋሙት ጽሕፈት ቤቶች በየደረጃው የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ አስተባባሪ ኮሚቴዎች፣ ጽሕፈት ቤቶችና የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች ይኖሯቸዋል፤

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ክልል ፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች በተጨማሪ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 መሠረት በሚመሠረት ክልል ውስጥ ሁሉ ፓርቲው የክልል ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

6) በየደረጃው ያሉ የፓርቲው መዋቅሮች በክልሉ ያሉ የፓርቲውን አባሎች በሙሉ የሚያሳትፉ እና የውሕዳን ቡድኖችን ውክልና የሚያረጋግጡ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 25. የክልል የፓርቲ ኮንፈረንስ የአሠራር ሥርዓት

1) የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ የከተማና የቀበሌ የፓርቲ ኮንፈረንሶች በየደረጃው የፓርቲ አባላት የፖለቲካ ግንባታ መድረክ ሆነው ያገለግላሉ፤

2) የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማና የቀበሌ የፓርቲ ኮንፈረንሶች ውክልናና ስብጥር በአባላት ብዛት ይወሰናል፤

3) የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማና የቀበሌ የፓርቲ ኮንፈረንሶች በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲ አስተባባሪዎች ጠሪነት የሚሰበሰብ ሆኖ የክልል በአንድ ዓመት አንድ ጊዜ፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳና የከተማ ኮንፈረንሶች በዓመት ሁለት ጊዜ፣ የቀበሌ በየሦስት ወሩ መሠረታዊ ድርጅት ደግሞ በየወሩ ኮንፈረንሳቸው ይካሄዳል፤

4) የክልል የቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን ኮሚቴዎች አጠቃላይ የሥራ ሂደት እና ፖለቲካዊ ሁኔታ በክልል የፓርቲ ኮንፍረንሶች ላይ ይገመገማል፡፡

አንቀጽ 26. የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት

1) በየደረጃው የፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

2) የፓርቲው አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶች በትክክል መተግባራቸውን ያረጋግጣል፤

3) የአባላቱን የፖለቲካ ብቃት እንዲዳብር ያደርጋል፤

4) በፓርቲው የጉባዔና የኮንፈረንስ ተሳትፎና ውክልና መመሪያ መሠረት ለፓርቲው ጉባዔና በየደረጃው ለሚካሄዱ ኮንፈረሶች አባላትን ይወክላሉ፤

5) የደረጃው ከፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴና ከኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን የሚቀርብለትን ዕቅድና የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ያጸድቃል፤

6) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ የፓርቲው ጉባዔ፣ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ና የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የሚያስቀምጡትን አጠቃላይ አቅጣጫና ውሳኔን ባከበረና አገራዊ የሆኑት የፓርቲው አደረጃጀቶች በሚሰጡት የአመራር ማዕቀፍ ውስጥ ባሉበት የአስተዳደር ቀጠና ውስጥ የፓርቲው ትልቁ የፖለቲካ መድረክ ይሆናል።

አንቀጽ 27. የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ

1) የክልል ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል።

2) የዞን፣ ወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ ከተማና ቀበሌ ፓርቲ ኮሚቴ አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተጠሪ ይሆናሉ።

3) የክልል የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ በየወሩ አንድ ጊዜ፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ ከተማና ቀበሌ በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።

4) በየደረጃው የሚገኙ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል።

ሀ) በቀጣናቸው የፓርቲ የፖለቲካና የድርጅት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራሉ፣

ለ) ከፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በተግባር ያውላሉ፣ ለሥራው ዝርዝር የአፈጻጸም ፕሮግራም አውጥተው በሥራ ላይ ያውላሉ።

ሐ) በየደረጃው የሚገኙትን የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ምደባ የውሳኔ ሐሳብ ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ጽሕፈት ቤት ያቀርባሉ፣ ሲጸድቅ ያሠማራሉ።

መ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ኮንፈረንሶች የሚያስቀምጡት አቅጣጫ የፓርቲው ጉባዔ፣ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴና የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የሚሰጡትን አመራርና ውሳኔ ባከበረ መልኩ ተጋባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል።

ሠ). በአገር አቀፍ ደረጃ ባሉ የፓርቲው መዋቅሮች የሚሰጡት አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ ክልላዊና አካባቢያዊ በሆነ ጉዳዮች የፖሊሲ ሐሳብ ያመነጫል።

5). የክልልና አካባቢያዊ ፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ቁጥር፣ ስብጥርና ምደባ የማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

አንቀጽ 28. የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች

1) የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶቹ በየደረጃው የፓርቲው የፖለቲካ፣ የድርጅትና የሕዝብ ግንኙነት ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ።

2) የጽሕፈት ቤቶቹ ተጠሪነት አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ይሆናል።

3) ጽሕፈት ቤቶቹ በሥራ አስፈጻሚ ወይም በየደረጃው ባሉት የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚሰየሙ ኃላፊና ምክትል ኃላፊዎች ሊኖሯቸው ይችላል።

4) የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፦

ሀ) የክልሉን የፓርቲ የፖለቲካና የድርጅት ሥራዎች ያቅዳሉ፣ያስፈጽማሉ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ፣

ለ) የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፤

ሐ) የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የሕዝብ ግንኙነትና ሌሎች ተግባሮችን ይፈጽማሉ፤

መ) በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ፓርቲውን ወክለው በየደረጃው ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ፤

ሠ) በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈጻጸም እና ዕቅዶችን በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሣሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃሉ፤

ረ) በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራሉ፣ ያስተዳድራሉ፣ ያሰናብታሉ፤

ሰ) በየደረጃው ባሉት የፓርቲ አደረጃጀቶች የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናሉ።

ሸ) ጽሕፈት ቤቶቹ በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርት አዘጋጅተው በየደረጃው ላሉት የፓርቲ ጽሕፈት ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ፤

አንቀጽ 29. የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ፦

1) የብልጽግና የሴቶች ሊግ ዋነኛ ተልዕኮ በፓርቲው ውስጥም ሆነ ውጭ የሴቶች መብቶችና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እና የኢትዮጵያና የህዝቦቿን ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ሴቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የመሪነት ሚና መጫወት ነው።

2) የሴቶችን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሴቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።

3) የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆኑ ሴቶች የብልጽግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ አባል መሆን

ይችላሉ፣

4) የብልጽግና የሴቶች ሊግ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሰራር መመሪያዎች ይኖረዋል።

5) የብልጽግና የሴቶች ሊግ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።

6) በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ የአመራር አደረጃጀት በትይዩ ለሚገኘው የብልጽግና የሴቶች ሊግ አደረጃጀት የቅርብ አመራርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።

7) ከፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ውጭ ባሉ በየደረጃው የሚገኙ የብልጽግና የሴቶች ሊግ የአመራር አደረጃጀቶች ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በትይዩ በሚገኙ የፓርቲው የአመራር አደረጃጀቶች ስብሰባዎች ያለ ድምጽ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

አንቀጽ 30- የብልጽግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ

1) የብልፅግና ወጣቶች ሊግ ዋነኛ ተልእኮ የኢትዮጵያና የህዝቦቿን ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ወሳኝ ሚና እንዲወጡ ለማስቻል እና የወጣቶችን ታሳትፎና ተጠቃሚነትና ለማረጋገጥ የማስተባበርና የመሪነት ሚና መጫወት ነው።

2) የወጣቶችን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የወጣቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።

3) ዕድሜው ከ14-35 ዓመት የሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የብልፅግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ አባል መሆን ይችላል። ዝርዝር አፈፃፀሙ የብልፅግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ በሚያወጣው መስፈርትና የአሰራር መመሪያ ይወሰናል።

4) ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የሊጉ አባል የፓርቲው አባል መሆን አለበት።

5) የብልፅግና የወጣቶች ሊግ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሰራር መመሪያዎች ይኖረዋል፤

6) የብልፅግና ወጣቶች ሊግ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።

7) በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ የአመራር አደረጃጀት በትይዩ ለሚገኘው የብልፅግና የወጣቶች ሊግ አደረጃጀት የቅርብ አመራርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።

😎ከፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ውጭ ባሉ በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አደረጃጀቶች ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በትይዩ በሚገኙ የፓርቲው የአመራር አደረጃጀቶች ስብሰባዎች

ያለ ድምፅ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

9) የፓርቲው ሙሉ አባል ያልሆነ የብልፅግና የወጣቶች ሊግ አባል በምርጫ በሚያዙ የፓርቲው የስራ ቦታዎች መወዳደር አይችልም፤ በልዩ ሁኔታ ካልተጋበዘ በስተቀር በፓርቲው የአባላት ወይም የአመራር ስብሰባዎች መሳተፍ አይችልም።

አንቀጽ 31. የፓርቲ ሴቶችና ወጣቶችና አደረጃጀት

1) በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ውስጥ ሴቶችና ወጣቶች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል አደረጃጀት ይኖራቸዋል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዝርዝር መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴ ይወጣል።

ምዕራፍ አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 32. የሥልጣን ዘመን

1) የፓርቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች የኃላፊነት ዘመን ጣራ ዐሥር ዓመት ይሆናል፤ የሌሎች አመራሮች የኃላፊነት ዘመን ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

2) የአመራርነት የእድሜ ጣሪያ ስድሳ አምስት ዓመት ይሆናል።

አንቀጽ 33. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1) በኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች የተሰየመው 11ኛው የኢሕአዴግ ጉባኤ ውሕደት እንዲፈጸም ለምክር ቤቱ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ግንባሩ ወደ ሀገራዊ ፓርቲ የተሸጋገረ በመሆኑ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶችና የአጋር የፖለቲካ ፓርቲዎች ውሕደት በዚህ ደንብ ተከናውኗል፤

2) የኢሕአዴግና የአጋር ድርጅቶች የነበራቸውን የተናጠል መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ወደ ብልጽግና ፓርቲ ተላልፏል፤

3) የብልጽግና ፓርቲ ጉባኤ እስኪካሄድ ድረስ የኢሕአዴግ ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ እንዲሁም የቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን የፓርቲው አመራር ሆነው ይቀጥላሉ፤

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአጋር ፓርቲዎች በምክር ቤት እና በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሳተፉ አባላት ብዛት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚወስነው ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።

5) የኢሕአዴግና የአጋር ድርጅቶች የሴቶች እና የወጣቶች አደረጃጀቶች የብልጽግና ፓርቲ አደረጃጀቶች ሆነው ይቀጥላሉ፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።

6) የኢሕአዴግና የአጋር ድርጅቶች አባላት ያለቅድመ ሁኔታ የብልጽግና ፓርቲ አባል ተደርገው ይቆጠራሉ።

አንቀጽ 34. የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች

የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች ከአባላት መዋጮ፣ በሀገሪቱ ሕግ መሠረት ከፓርቲው ደጋፊዎች እና ወዳጆች ከሚገኝ ድጋፍ ይሆናል።

አንቀጽ 35. የፓርቲው የሰው ሐብት፣ ንብረት፣ ፋይናንስና የሂሳብ መዛግብት የአሠራር ሥርዓት

1) የፓርቲው የሰው ሐብት፣ ፋይናንስና ንብረት ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚተዳደር ይሆናል፤

2) ፓርቲው የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣ በውስጥና በውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ያስመረምራል።

3) በፓርቲው ገንዘብና ንብረት ላይ የመወሰን ሥልጣን ማዕከላዊ ኮሚቴው ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ 36. በፓርቲው ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት

1) በፓርቲው አካላት ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በዚህ ደንብ ውስጥ በተደነገጉ የአሠራር ሥርዓቶች መፈታት አለባቸው፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መፈታት ካልቻለ በሀገሪቱ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ሕግና በሌሎች ሕጎች መሠረት ይፈታል።

አንቀጽ 37. የፓርቲው ውሕደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር ሥርዓት

1) ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውሕደት ወይም ቅንጅት ወይም ግንባር መፍጠር ይችላል፣

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ መሠረት መሆኑን ማዕከላዊ ኮሚቴ ያረጋግጣል፤

3) ማዕከላዊ ኮሚቴው በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ መሠረት መሆኑን ካረጋገጠና የውሕደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሐሳቡን ከተቀበለው በኋላ ለፓርቲው ጉባኤ አቅርቦ ያስጸድቃል፤

አንቀጽ 38. የፓርቲ መፍረስ

የፓርቲው ጉባኤ ቢያንስ በሦስት አራተኛ (3/4) ድምፅ ፓርቲው እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል።

አንቀጽ 39. የፓርቲው አማካሪ የመማክርት ጉባኤ

1) ፓርቲው ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎቹን ለማሳካት የተለያዩ ሞያ ያሏቸውን ምሁራንና ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈ የፓርቲው የመማክርት ጉባኤ በፕሬዚዳንቱ አቅራቢነት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል።

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልል የፓርቲ ጽ/ቤት የፓርቲ ሰብሳቢ አቅራቢነት የክልል አስተባባሪ ኮሚቴዎች የመማክርት ጉባኤ ሊያቋቁሙ ይችላሉ።

አንቀጽ 40. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የበላይነት

1) መተዳደሪያ ደንቡ የፓርቲው የበላይ ሕግ ስለሆነ በፓርቲው አካላትና አባላት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል።

2) በመተዳደሪያ ደንቡና በሌሎች የፓርቲ ሰነዶች መካከል ግጭት ሲያጋጥም የዚህ መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች የበላይነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ 41. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ለተለያዩ አካላት የተሠጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ይህን ደንብ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

አንቀጽ 42. መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻል፣ መቀየርና ስለመሻር

1) ይህን መተዳደሪያ ደንብ ሊያሻሽል፣ ሊቀይርና ሊሽር የሚችለው የፓርቲው ጉባኤ ብቻ ነው፤

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመተዳደሪያ ደንቡ የማሻሻያ ሐሳብ ሊቀርብ የሚችለው፦

ሀ) በፕሬዚዳንቱ ወይም

ለ) በማዕከላዊ ኮሚቴው 1/3 ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም

ሐ) በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም

መ) በቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን አባላት 1/2 ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበ የማሻሻያ ሐሳብ ለፓርቲው ጉባኤ መቅረብ የሚችለው በማዕከላዊ ኮሚቴው በአብላጫ ድምፅ ድጋፍ ካገኘ ነው።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት በማዕከላዊ ኮሚቴ በቀረበው የማሻሻያ ሐሳብ ላይ የፓርቲው ጉባኤ በአብላጫ ድምፅ ከወሰነ መተዳደሪያ ደንቡ ይሻሻላል፡፡